

# ሶስቱ ቆራጥ ወጣቶች

- ንጉስ ናቡከደነፆር እጅግ በጣም ግዙፍ የወርቅ ምስል አሰራ። የዚህ የወርቅ ምስል ርዝመቱ 60 ክንድ ሲሆን ስፋቱም እንዲሁ 60 ክንድ ነበር። ንጉሱ ይህን የወርቅ ምስል ካሰራ በኋላ ሕዝቡን "የሙዚቃ ድምፅ በሰማችሁ ጊዜ ወድቃችሁ ላቆምኩት የወርቅ ምስል ስገዱ፤ ማንም የሙዚቃ ድምፅ ሰምቶ ለወርቁ ምስል የማይሰግድ ቢኖር በኃይል በሚቀጣጠል እሳት ውስጥ ይጣላል።" አላቸው።

- በአንድ ወቅት እስራኤላውያን ተማርከው ወደባቢሎን ተወስደው ነበር። አንዳንዶቹም የወርቁ ምስል በተሰራበት ጊዜ በባቢሎን ይኖሩ ነበር። ከእነኚህ መካከልም በምድረ ባቢሎን ገዢ መሆን የቻሉ ሶስት ወጣቶች ነበሩ። ስማቸውም ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብደናጎም ይባላል። እነኚህ ሶስት ወጣቶች እውነተኛውን እግዚአብሔርን ብቻ ያመልኩ ስለነበር ንጉስ ናቡከደነፆር ላቆመው ለወርቁ ምስል አንሰግድም አሉ። ንጉሱንም "የምናመልከው አምላክ ከሚነደው እሳት ሊያድነን ይችላል። ነገር ግን ባያድነንም እንኳን አማልክትህን አናገለግልም፤ ላቆምከው ለወርቁ ምስልም አንሰግድም!" አሉት። ምንኛ ቆራጦች ናቸው!

- ንጉሱ በወጣቶቹ መልስ እጅግ ስለተበሳጨ እሳቱን ሰባት እጥፍ እንዲያነዱት አዘዘ። ሶስቱ ወጣቶችም ታስረው ወደእሳቱ ውስጥ እንዲጣሉ አደረጋቸው። እሳቱ እጅግ ብርቱ ስለነበር ሶስቱን ወጣቶች እሳት ውስጥ የወረወሯቸው ሰዎች በእሳቱ ወላፈን ተቃጥለው ሞቱ።
  ነገር ግን ንጉሱ ወደ እሳቱ ሲመለከት የሚያስደንቅ ነገር አየ። ወደ እሳት የጣላቸው ወጣቶች እስራታቸው ተፈትቶ በእሳት ውስጥ ሲመላለሱ አየ። ደግሞም ሶስት ሆነው ተጥለው ነበር። አሁን ግን አራተኛ ሰው ከእነርሱ ጋር አብሮ ታየ። ስለዚህ ንጉሱ እንዲህ አለ " እሳት ውስጥ የጣልናቸው ሶስት ሰዎች ብቻ አልነበረም ወይ? አሁን ግን የተፈቱና ምንም ጉዳት ሳይደርስባቸው በእሳቱ ውስጥ የሚራመዱ አራት ሰዎችን አያለሁ። አራተኛውም ሰው ሰማያዊ ፍጡር ይመስላል።"

- ከዚያም የወጣቶቹን ስም ጠርቶ ከእሳቱ ውስጥ እንዲወጡ ጠየቃቸው። ከእሳቱ ውስጥ ሲወጡም አንዳችም ጉዳት አልደረሰባቸውም። ፀጉራቸው አልተቃጠለም። እንዲሁም ምንም የጭስ ሽታ አልነበረባቸውም።

- ❋ ከዚያም ንጉሱ እንዲህ የሚል አዋጅ አወጣ። “ማንም በግዛቴ የሚኖር ሁሉ ከዛሬ ጀምሮ የሲድራቅን፣ የአብደናጎምንና የሚሳቅን አምላክ ብቻ እንዲያከብር። ምክንያቱም የሚያድን እውነተኛ አምላክ እርሱ ብቻ ነው።”

የሶስቱ ቆራጥ ዕብራውያን ወጣቶች ታሪክ በመፅሐፍ ቅዱስ በትንቢተ ዳንኤል በምዕራፍ 3 ውስጥ ይገኛል።

http://gardenofpraise.com